# አብዮታዊት ኢትዮጵያ 19




ሌ/ ኰሎኔል ዳንኤል አስፋው፣



ዶክተር ሰናይ ልኬ ።

"ለውጊያ ዘመቻ–
የምታቀርበው ሀሳብ
የምታዘጋጀው ዕቅድ
የምታሳልፈው ውሳኔ
የምትሰጠው ትዕዛዝ–
በተዋጊው
ሠራዊት
ደም
የሚጻፍ ነው።

ዳንኤል አስፋው


ጥር ፴ ፲፱፻፷፱ ዓ.ም.

**ለውይይት መነሻ**

አብዮታዊት ኢትዮጵያ ከቍጥር ፬ ጀምሮ «ለነማርክስ ፍልስፍና አጭር መግቢያ» በሚል ርእስ ሥር በተከታታይ ትምህርታዊ የሆኑ የፍልስፍና ጽሑፎች ታቀርባለች ። እነዚህ ጽሑፎች የማርክሲዝምን ርእዮተ ዓለም ገና ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚተዋወቁ የውይይት ክበቦች መነሻ ሃሳቦች እንደሚሰጡ ሆነው የቀረቡ ናቸው።

# የወዝአደሩ አምባገነንነት

፲፬ኛ ትምህርት ከን.ዓ.

የካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር በፈረሰ ማግሥት የኮሙኒስት ሥርዓተ ማኅበር አይመሠረትም። መደቦች አይደመሰሱም ። ስለሆነም መደቦች እስካሉ ድረስ አንዱ መደብ ሌላውን የሚጨቁንበት የማስገደጃ መሣሪያ ያስፈልገዋልና ከካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር ወደ ኮሙኒስት ሥርዓተ ማኅበር ባለው የመሸጋገሪያ ወቅት መንግሥት ይኖራል ።

« በካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበርና በኮሙኒስት ሥርዓተ ማኅበር መሐከል ያኛው ወደዚህኛው የሚለወጥበት የአብዮታዊ ሽግግር ወቅት ይኖራል ። ከዚህም ጋር መንግሥት ከወዝአደሩ አብዮታዊ አምባገነንነት ሌላ ነገር መሆን የማይቻልበት የፖለቲካ ሽግግር ወቅት ይኖራል ። »

ይህ የወዝአደር አምባገነንነት የሚንፀባረቅበት መንግሥት እንደማንኛውም ዓይነት መንግሥት የመደብ መሣሪያ ነው ። ነገር ግን ይህ መንግሥት በታሪክ ከቀደሙት ከሌሎቹ የመንግሥት ዓይነቶች በግልጽ የሚለይባቸው ብዙ ነጥቦች አሉ። አንደኛ ይህ መንግሥት ምንም እንኳን የመደብ ጥቅም ማረጋገጫና ማጽደቂያ የሆነ የማስገደጃ ድርጅት ቢሆንም በታሪክ በመጀመሪያ ጊዜ የብዙኃኑን ጥቅም ለማረጋገጥ ፤ ይህንን የብዙኃኑን ጥቅም የ ሚፃረሩ መደቦችን ጨቁኖ ለመያዝ የቆመ ባጭሩ የብዙኃኑ እንጂ እፍኝ የማይሞሉ ጨቋኞችን ጥቅም ለመጠበቅ የቆመ መንግሥት አይደለም ።

ሁለተኛ ይህ የወዝአደር አምባገነንነት መንግሥት እንደሌሎቹ የአንድን መደብ ጥቅም «ለዘለዓለም » ለማንፀባረቅ ሳይሆን መደቦችን በሙሉ አጥፍቶ መደብ አልባና ጭቆና የሌለበት ሥርዓት ለመመሥረት የ ሚታገል መንግሥት ነው።

ስለሆነም የዚህ መንግሥት የመጀመሪያ መልኩ አድኃርያን ከሥልጣን ከተወገዱ በኋላ ያለ የሌለ ኃይላቸውን አስተባብረው አብዮቱን ቀልብሶ እንደገና ወደ ሥልጣን ለመመለስ የሚያደርጉትን ትግል ለመቋቋምና ለመደምሰስ የሚችል ፤ ለዚህም በቀድሞ ገዥ መደቦች ላይ ጦርነት ያወጀ መንግሥት መሆን አለበት ።

« የወዝአደሩ አምባገነንነት አዲሱ መደብ ከሱ ይበልጥ ኃይለኛ ከሆነ የመደብ ጠላቱ ጋር የሚያካሂደው ቆራጥና የማያወላውል ጦርነት ነው። ( ሌኒን )

ነገር ግን የወዝአደሩ አምባገነን መንግሥት ከበርቴውን በመደምሰስ ብቻ አያቆምም ። አንዱ ሌላው ዋና ተግባሩ ሶሻሊዝምን ለመገንባት አስፈላጊ የሆነውን የኢኮኖሚ መሠረት መጣል ነው። አሁንም እንደገና ሌኒንን ብንጠቅስ እንደሚከተለው ይናገራል ።

« የወዝአደሩ አምባገነንነት በበዝባዥ መደቦች ላይ የሚካሄድ ዓመፅ ብቻ አይደለም ። እንዲያውም ዋናው ይዘቱ እንኳን ይኸ ዓመፅ አይደለም ። ወዝአደሩ ከካፒታሊዝም ዘመን የተሻለ የምርት ቅንብርን ከሥራ ላይ ያውላል ። . . . የኮሙኒዝም የተሟላና የማይቀር ድል ዋስትናውና ምንጩ እዚህ ላይ ነው » ( ሌኒን )

በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ የወዝአደሩ አምባገነንነት የመደብ ጦርነትን ማካሄድ ፣ ኢኮኖሚውን መገንባት ብቻ ሳይሆን ሠርቶ አደሩን ሕዝብ የማስተማርና የማንቃት ተግባርም አለበት ። ይህ እንዲያውም በቀድሞ ገዥ መደቦች ላይ ከሚካሄደው ግልጽ የሆነ ጦርነት ይበልጥ የተወሳሰበና አስቸጋሪ ተግባር ነው ። ሰፊውን ሕዝብ በተለይ ገበሬውን እንቅቶ የሶሻሊዝምን ጐዳና እንዲቀበል ለማድረግ ኃይል ሳይሆን ረዥምና ብዙ ትዕግሥት የሚጠይቅ የማስተማር ሥራ ይጠይቃል ።

እንግዲህ ከላይ እንዳልነው ይህ የወዝአደር አምባገነን መንግሥት በቀድሞ ገዥ መደቦች ላይ የፈላጭ ቆራጭነት ጠባይ አለው ። ይህ ማለት ግን ይህ መንግሥት ዲሞክራሲን አያውቅም ፣ ዲሞክራሲያዊ አይደለም ማለት አይደለም ። ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ነው ። ነገር ግን ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ እንደተነገረው ዲሞክራሲ ሁሉ ጊዜ የአንዱ መጨቆኛ የሌላው መደብ መገልገያ መሣሪያ እንጂ ለሁለት ጠላት መደቦች በአንድ ላይ እኩል የሚያገለግል አይደለም ። ስለሆነም በቀድሞ ጊዜ የነበሩትን መንግሥታት ወይንም አሁን በካፒታሊስት አገሮች የሚገኙ መንግሥታት « ዲሞክራሲያዊ » ተብለው ሲጠሩ የነሱ ዲሞክራሲያዊነት ለጥቂት የገዥ መደብ አባላት ነበር ። ነውም ። የወዝአደሩ አምባገነን መንግሥትም ዲሞክራሲያዊ ነው ሲባል ለሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች ሳይሆን ለወዝአደሩና ለአጋሮቹ ነው ማለት ነው ። የከበርቴዎች መንግሥት ለነሱ ዲሞክራሲያዊ የሆነውን ያህል በወዝአደሩና በተቀረው ሰፊ ሕዝብ ላይ የፈላጭ ቆራጭነት የአምባገነንነት መልክ አለው ። የወዝአደሩ መንግሥት አምባገነንና ፈላጭ ቆራጭ ሲባል አምባገነንነቱ በቀድሞ ገዥ መደቦች ላይ ሁኖ ለተቀረው ለብዙኃኑ ሰፊ ሕዝብ ግን ዲሞክራሲያዊ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል ። በዚህ የተነሣ የወዝአደሩ አምባገነንነት በኅብረተሰቡ የሚያሰፍነው ዲሞክራሲ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለው አብዛኛው ሕዝብ የሚሳተፍበትና ለአብዛኛው ሕዝብ ከሥራ ላይ የሚውል ዓይነት ዲሞክራሲ ነው ማለት ነው ።

የወዝአደሩ አምባገነንነት ሲባል ወዝአደሩ የቀድሞ ገዥ መደቦችን ደምስሶ አዲስ ሥርዓት ለመገንባት በሚያደርገው ትግል ይህ መደብ ብቻውን ይታገላል ማለት አይደለም ። እንደ እርሱው ብዝበዛ ያንገፈገፋቸውና የበዝባዦችን ቀንበር ታግለው ለመጣል የሚፈልጉ በተለይም የገጠርና የከተማ ሌሎች ሠርቶ አደሮችና ድኃ ገበሬዎች ከወዝአደሩ መደብ ጋር ኅብረት መሥርተው ይታገላሉ ።

በዚህ ኅብረት ላይ የተመሠረተው የወዝአደሩ አምባገነን መንግሥት ለወዝአደሩና ለተቀሩት ለፍቶ አደሮች በሙሉ የተሟላ ዲሞክራሲን ያሰፍናል ። የምርት ኃይሎች በሙሉ በወዝአደሩ እጅ ስለሆኑ ፣ የኢኮኖሚውን አመራር የያዘው እርሱ ነው ። ስለሆነም የወዝአደሩ መንግሥት ለእያንዳንዱ ሠርቶ አዳሪ የኑሮ ዋስትና ይሰጣል ። ት/ቤቶችን ፣ ሆስፒታሎችን ፣ የባሕል ቤቶችን ፣ የዕረፍት ቦታዎችን ሁሉ ለሠርቶ አደሩ ጥቅም ያውላቸዋል ። ለለፍቶ አደሩ ሕዝብ የታወቀው የዲሞክራሲ መብት ከወረቀት እንዳያልፍ የወዝአደሩ መንግሥት ለሕዝቡ መገልገያ ማተሚያ ቤቶችን ፣ ወረቀት ፣ ሬዲዮ ፣ የመሰብሰቢያ አዳራሽ የመሳሰሉትን ሁሉ ስለሚፈቅድ የንግግር የመጻፍ. . . .ነፃነት በርግጥ ከሥራ ላይ ይውላሉ ።

ለፍቶ አደሩ ሕዝብ በዚህ መልክ በሀገሩ የፖለቲካ ሕይወት በሰፊው ይሳተፋል ። በዚህ መልክ በልዩ ልዩ ድርጅቶች አማካኝነት በሚሊዮን የሚቆጠረው ሰፊ ሕዝብ ተሳትፎውን ስለሚያረጋግጥ ሌኒን እንዳለው የወዝአደሩ አምባገነን መንግሥት ከየትኛውም የከበርቴ መንግሥት ሚሊዮን ጊዜ ይበልጥ ዲሞክራሲያዊ ነው ።